
ፈጣሪ ተናገረ
ትምህርት 1 for መስከረም 3, 2026





"ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ዓይነትና በብዙ ጎዳና ለአባቶቻችን በነቢያት ተናግሮ፥ ሁሉን ወራሽ ባደረገው ደግሞም ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ በዚህ ዘመን መጨረሻ ለእኛ ተናገረን፤"

(ዕብራውያን 1:1-2)

እግዚአብሔርን *በቀጥታ* አናግራችሁት ታውቃላችሁ? የእግዚአብሔርን ቃላት መስማት ችላችሁ ታውቃላችሁ? ግልጽ የሆነው መልስ: “አልሰማንም” ነው።

እግዚአብሔርን ማናገር የምንችለው ቀጥተኛ ባልሆኑ መንገዶች ብቻ ነው (ለምሳሌ ጸሎት፣ መጽሐፍ ቅዱስ፣ ነቢያት …)

እግዚአብሔርን በቀጥታ ማናገር ያልቻልንበት ምክንያት ምንድን ነው? ይህ ሁኔታ ከጥንትም የነበረ ነውን? አንድ ቀን ፊት ለፊት ማናገር እንችል ይሆንን?






1. እግዚአብሔር በመጀመሪያ ሰውን ያናግር የነበረው እንዴት ነበር?
2. የሰው ልጅ ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር ያቆመው ለምንድን ነው?
3. እግዚአብሔር ግንኙነቱን ለማደስ የሞከረው እንዴት ነው?
4. አሁን ከእግዚአብሔር ጋር በቀጥታ መነጋገር የማንችለው ለምንድን ነው?
5. ዛሬ ከእግዚአብሔር ጋራ መነጋገር የምንችለው እንዴት ነው?

# እግዚአብሔር በመጀመሪያ ሰውን ያናግር የነበረው እንዴት ነበር?

"እግዚአብሔር አምላክም ሰውን እንዲህ ብሎ አዘዘው፡- ከገነት ዛፍ ሁሉ ትበላለህ፤ " (ዘፍጥረት 2:16)







እግዚአብሔር በመጀመሪያ ምድርን ሲፈጥራት የሰው ልጆች መኖሪያ እንድትሆን ነበር (ኢሳ 45:18)።

ሁሉን ነገር ካዘጋጀ በኋላ አዳምን ከምድር አፈር አበጀው (ዘፍ 2:4-7)።





በዚያው ቀን ሔዋንን ከአዳም የጎን አጥንት ፈጠራት (ዘፍ 2:18፣ 21-22)።

ከዚያም የሰው ልጅ ምሉዕ ሆኖ በተፈጠረለት አዲስ ዓለም ውስጥ ለመኖር ዝግጁ ሆነ (ዘፍ 1:27)።

# እግዚአብሔር በመጀመሪያ ሰውን ያናግር የነበረው እንዴት ነበር?

"እግዚአብሔር አምላክም ሰውን እንዲህ ብሎ አዘዘው፦ ከገነት ዛፍ ሁሉ ትበላለህ፤ " (ዘፍጥረት 2:16)






በዚህ ሂደት ውስጥ በእግዚአብሔርና በአዳም መካከል ብዙ ግንኙነት ነበር:

- በኤደን ስለሚሰራው ስራ መመሪያን ሰጥቶት ነበር (ዘፍ 2:15)።
- ገደቡንም አመልክቶት ነበር (ዘፍ 2:16-17)።
- እንስሳትን እንዲሰይም ሰጥቶት ነበር (ዘፍ 2:19)።
- ሔዋንን ለእርሱ አስተዋውቆ በትዳር እንዲጣመሩ አድርጎ ነበር (ዘፍ 2:22-24)።

# እግዚአብሔር በመጀመሪያ ሰውን ያናግር የነበረው እንዴት ነበር?

"እግዚአብሔር አምላክም ሰውን እንዲህ ብሎ አዘዘው፡- ከገነት ዛፍ ሁሉ ትበላለህ" (ዘፍጥረት 2:16)

እግዚአብሔር ለአዳምና ለሔዋን እንዴት መኖር እንዳለባቸውና ምን መመገብ እንዳለባቸው መመሪያ ሰጥቷቸው ነበር (ዘፍ 1:28-29)።

እርስ በራሳቸውና ከሌሎችም ፍጥረታት ጋር መነጋገር የሚችሉ ማህበራዊ ፍጡሮች አድርጎ ፈጠራቸው (ለምሳሌ ከመላዕክት ጋር መነጋገር ይችላሉ)።

ከዚያም ደግሞ አንድን ቀን ሙሉ አብሯቸው ለማሳለፍ የሰንበትን ቀን ፈጠረ።

በኤድን ገነት ውስጥ  ቀኑ ሲመሻሽ ሁልጊዜ ሊገናኛቸውም ይመጣ ነበር (ዘፍ 3:8)።









# የሰው ልጅ ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር ያቆመው ለምንድን ነው?

"እርሱም አለ፦ በገነት ድምፅህን ሰማሁ፤ ዕራቁቴንም ስለ ሆንሁ ፈራሁ፥ ተሸሸግሁም።" (ዘፍጥረት 3:10)







አዳምና ሔዋን የተፈጠሩት በነፃነት የመምረጥ ችሎታን ይዘው ነበር። እግዚአብሔር ይህንን ነፃነታቸውን እንዲለማመዱ ሁሉን ነገር አሳልፎ ሰጣቸው ነገር ግን አንዲት ዛፍን ለራሱ ብቻ ገድቦ አስቀመጠ (ዘፍ 2:16-17)።



በዚያው ዛፍ ላይ ፈታኙ በእባብ መልክ ተመስሎ አዳምንና ሔዋንን ለመጥቀም እንደመጣ እያስመሰለ ተከታታይ ውሸቶችን እንዲህ ብሎ ለሔዋን ነገራት፣ እርሷም ለአዳም አስተላለፈችው: መሞትን አትሞቱም ("የማትሞቱ ናችሁ")፤ አማልክት ትሆናላችሁ ("እንደ እግዚአብሔር ትሆናላችሁ")፤ እግዚአብሔር እውነቱን ከእናንተ ደብቋል ("እግዚአብሔር እያወቀ ደብቋችኋል") (ዘፍ 3:1-5) አላቸው።

ሔዋንም ስለ ዛፉ ፍሬ ሰይጣን በነገራት ነገር እየተደነቀች ከፍሬው ቀጥፋ በላች፣ አዳምንም አነሳስታ እንዲበላ አደረገችው (ዘፍ 3:6)።



በዚያን ሰዓት የሸፈናቸው የክብር ልብስ ተገፈፈ፣ ራቁታቸውን መሆናቸውንም አስተዋሉ፣ እናም ስህተታቸውን ለመሸፈን መፍትሄዎችን መፈለግ ጀመሩ (ዘፍ 3:7)።

ቀጥሎ ያደረጉት አሳዛኝ ድርጊት ባለመታዘዛቸው እጅግ ስለተጸጸቱ ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር አለመፈለጋቸው ነው (ዘፍ 3:8)።

# እግዚአብሔር ግንኙነቱን ለማደስ የሞከረው እንዴት ነው?

"እግዚአብሔር አምላክም አዳምን ጠርቶ፦ ወዴት ነህ? አለው።" (ዘፍጥረት 3:9)



እግዚአብሔር አዳምና ሔዋን መተላለፋቸውን ቢያውቅም እንደ ልማዱ ሊያነጋግራቸው ወደ እነርሱ ቀረበ። እንደወትሮው እርሱን ሊገናኙ በደስታ ከመምጣት ይልቅ ስለተደበቁ እግዚአብሔር ወደ እርሱ እንዲመጡ ጠራቸው (ዘፍ 3:8-9)።



ምንም እንኳን ከእግዚአብሔር ጋር ሊነጋገሩ ባይፈልጉም እርሱ ግን ሊገናኛቸው ፈልጎ ነበር። ንስሃ ገብተው እንዲመለሱ ኃጥያተኞቹን ከነኃጥያታቸው ቀረባቸው እንጂ ሕብረት እንዳያደርጉ አላባረራቸውም (ዘፍ 3:10-11)።



እግዚአብሔር ከብዙ ምዕተ ዓመታት በኋላ በንስሃ ሊመልሰው አይኑን በሌላ ኃጥያተኛ ላይ ጥሎ ነበር፡ ይህም ኃጥያተኛ ጴጥሮስ ነበር (ሉቃ 22:61-62)።

እንደ ጴጥሮስ ኃጥያታቸውን ከማመን ይልቅ አዳምና ሔዋን በእግዚአብሔር ፊት ምክንያትን መደርደርና እርስ በራሳቸው መካሰስ ጀመሩ (ዘፍ 3:12-13)።



ዛሬም እኛ ሰዎች ተመሳሳይ ባህሪ ይታይብናል። ኃጥያታችንን ሙጥኝ ብለን ለራሳችን ሰበብ እንደረድራለን። ነገር ግን ኃጥያት ከኛ ጋር "ቢጣበቅ" እንኳ እግዚአብሔር ሁልጊዜ ሊመልሰን ይፈልጋል፤ እናም "ወደ እኔ ኑ" እያለ ይጣራል (ኢሳ 55:3)።

# አሁን ከእግዚአብሔር ጋር በቀጥታ መነጋገር የማንችለው ለምንድን ነው?

**“አዳምንም አስወጣው፥ ወደ ሕይወት ዛፍ የሚወስደውንም መንገድ ለመጠበቅ ኪሩቤልንና የምትገለባበጥ የነበልባል ሰይፍን በዔድን ገነት ምሥራቅ አስቀመጠ።” (ዘፍጥረት 3:24)**



እግዚአብሔር በኃጥያት ለወደቁት ጥንዶች የኃጥያታቸውን ውጤት አሳያቸው፤ ከውጤቶቹም አንዱ ከኤደን ከወጡ በኋላ ከእግዚአብሔር ጋር በቀጥታ መነጋገር አለመቻላቸው ነው (ዘፍ 3:16-24)።

**የኃጥያት ውጤት:**

**ለሔዋን**
– ስትወልድ ምጧ ይበዛል
– ለአዳም ትገዛለች

**ለአዳም**
– በስራ ይደክማል
– መሬትን ያርሳል

**ለሁሉም**
– ይሞታሉ
– ከእግዚአብሔር ይለያሉ



እግዚአብሔር ግን የኃጥያትን ውጤት ከመናገሩ በፊት መፍትሄውን አቀረበላቸው: የሔዋን ዘር የሰይጣንን ሃይል አክትሞ የሰውን ዘር ሁሉ እንደሚመልስም ነገራቸው (ዘፍ 3:15)።

እግዚአብሔር እንዴት ሊቤዠን እንዳለ በነቢያት በኩል ሲናገር ቆይቶ ነበር: እግዚአብሔር እራሱ ሰው ሆነ፣ የኃጥያታችንን ሞት ተቀጣ፣ በሶስተኛውም ቀን ተነሳ፣ ለእኛም የዘላለም ሕይወትን ሰጠን (ኢሳ 9:6፣ 53:6፣ 10-11)።

ገና ኃጥያት ከመሰራቱ የአዳኙም ተስፋ እንዲሁ ታወጀ።



# ዛሬ ከእግዚአብሔር ጋራ መነጋገር የምችለው እንዴት ነው?





“አንተም፥ የሰው ልጅ ሆይ፥ ለእስራኤል ቤት ጕበኛ አድርጌሃለሁ፤ ከአፌ ቃሌን ስማ ከእኔም ዘንድ አስጠንቅቃቸው።” (ሕዝቅኤል 33:7)



እግዚአብሔር ዛሬ ከእኛ ጋር ለመነጋገር ሁለት “ማጣቀሻ መጻሕፍትን” ጽፎልናል: እነርሱም ፍጥረትና መጽሐፍ ቅዱስ ናቸው (ሮሜ 1:20፣ 2ጢሞ 3:15)።

ፍጥረት ስለ ፈጣሪው ቢናገረንም እንኳ ኃጥያት በብዙ አበላሽቶታል። መጽሐፍ ቅዱስ ግን ነቢያት ከእግዚአብሔር በተቀበሉት መልዕክቶች ውስጥ ያስተላለፉትን ግልጽና ቀጥተኛ መመሪያዎችን ይዟል። ደግሞም በኢየሱስ ሕይወትና አገልግሎት ውስጥ ፍጹም የሆነውን የእግዚአብሔር መገለጥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እናገኛለን (ዕብ 1:1-2)።





በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ማን እንደሆንን ፣ ከየት እንደመጣን እና ወዴት እንደምንሄድ እናውቃለን። እግዚአብሔር ለሕይወታችን ያለውን እቅድ እንደዚሁ በዚያ ውስጥ እናኛለን።

በተጨማሪም እግዚአብሔር በጸሎት (መዝ 5:2)፣ በመላዕክት (የሐዋ 8:26)፣ በነቢያት (ኢዮ 2:28) እና በተለይ ደግሞ በመንፈስ ቅዱስ በኩል ያናግረናል (ዮሐ 14:26)።



“በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ትብብር ሊኖር ነበር። ነገር ግን ይህ ዕቅድ በአዳም መተላለፍ የተነሳ በእጅጉ ተደናቅፎ ነበር። ሰው በሰይጣን ወደ ኃጥያት ስለተመራ ሳይወድቅ በፊት እንደነበረው ከጌታ ጋር መነጋጋር አልቻለም።

ከውድቀት በኋላ ክርስቶስ የአዳም አስተማሪ ሆነ። እግዚአብሔርን ወክሎ ከሰው ጋር በመገናኘት የሰውን ዘር ወዲያውኑ ከመጥፋት አዳነው። የመካከለኛነትን ሚና በፈቃዱ ወሰደ። አዳምና ሔዋን ወደ ቀደመው ስፍራቸው እንዲመለሱ የፈተና ጊዜ ተሰጣቸው፤ በዚህም እቅድ ከእነርሱ ቀጥሎ የሚመጣ ትውልድ ሁሉ ተካትቶ ነበር።

የእግዚአብሔር ልጅ ሥርየትን ባያስገኝ ኖሮ ከእግዚአብሔር ወደ ሰው ምንም አይነት በረከት ወይም መዳን ሊተላለፍ አይችልም ነበር። እግዚአብሔር ሕጉ እንዲከበርለት ቀንቶ ነበር። ያን ሕግ ስለተላለፉ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል አስፈሪ መለያየት ተፈጥሮ ነበር። አዳም ሳይወድቅ በፊት ከፈጣሪው ጋር ቀጥተኛ፣ ነፃ እና ደስተኛ ሕብረት ተፈቅዶለት ነበር። አዳም ከተላለፈ በኋላ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር የሚገናኘው በክርስቶስና በመላዕክት በኩል ብቻ ነበር።”

EGW (Conflict and Courage, January 14)

# አባሪ: የኤለን ጂ. ኋይት የህይወት ታሪክ



ከዩኒስ እና ሮበርት ሀርመን ስምንት ልጆች የመጨረሻ የሆኑት ኤለን ጉልድ እና ኤልሳቤጥ ሀርመን እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በሕዳር 26 /1827 በአሜሪካ ሜይን በተባለ ግዛት ውስጥ ግሮሃም በተባለች ከተማ ተወለዱ።

ብዙም ሳይቆይ ይህ ቤተሰብ የኮፍያ ስራ ገበያውን ለማስፋት በሜይን ዋና ከተማ ወደ ነበረችው ወደ ፖርትላንድ ሄዱ።

ኤለን ኋይት ገና ዘጠኝ አመቷ ሳለች አንድ የክፍል ጓደኛዋ ድንጋይ ወርውሮ ፊቷ ላይ ጉዳት አድርሶባት ነበር። በዚህ ጉዳት ሳቢያ በደረሰባት ከባድ ተጽዕኖ ከትምህርት ቤት እንድትወጣና የተገደበ ማህበራዊ መስተጋብር እንዲኖራት ተገድዳ ነበር።





ይህ ቤተሰብ የዊሊያም ሚለርን ትምህርት ሲቀበሉ ኤለን ደግሞ በ1842 በሜቶዲስት ቤተክርስቲያን ውስጥ ተጠመቀች።

ነገር ግን ኤለን እንደጠፋች ይሰማት ነበር፤ ለመዳንም ብቁ እንዳልሆነች ታምን ነበር። ፓስተር ሌዊ ስቶክማን ካገኛት በኋላ ግን የእግዚአብሔርን እውነተኛ ፍቅር እንድትረዳ አግዟት ነበር።



ከዚያን ጊዜ አንስቶ ከኢየሱስ ጥልቅ ፍቅር ያዛት፣ በቀረው ዘመኗም እያገለገለችው አለፈች።